# የግንቦት 7 ድምጽ

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 205 ሚያዝያ 11 2004 ገጽ 1


የሁለቱ ሃይማኖቶች ምዕመናን ሊጋራ መብቶቻቸውና ሊጋራ አገር በአንድነት መቆማቸው በመለስ ዜናዊና ቡድኑ አማካይነት እየደረሰብን ያለውን አዋራጅ የባርነት ጊዜ ያሳጥራል፤ ወደ ነፃነት የምናደርገውን ጉዞ ያፋጥናል። ከዚህም በተጨማሪ ከመለስ በኋላ በምትኖረው ኢትዮጵያችን ውስጥም ህዝቧ ተቻችሎና ተፋቅሮ የሚኖር መሆኑ ከአሁኑ ማስተማመኛ ይሰጠናል።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## ዘረኛው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በፈጠረው ኢኮኖሚያዊ ችግር ክፉኛ በተመታው አድስ አበባ ከተማ ውስጥ "ተነሱ የሚል ጥሪ ወረቀት" በስፋት እየተበተነ መሆኑ ተገለጸ

የኢትዮጵያ ወጣቶች ተሰፋ ድርጅት በሚል ስያሜ የሚንቀሳቀስ አንድ ቡድን በአዲስ አበባ በተለያዩ አካባቢዎች ተነሱ የሚሉ የጥሪ ወረቀቶችን መበተኑን የግንቦት 7 ዘጋቢ ከአዲስ አበባ በላከው ሪፖርት ገለጸ።

እንደዘጋቢያችን ሪፖርት በተለያዩ የአዲስ አበባ ከተሞች ውስጥ በተበተኑ ወረቀቶች ላይ የሰፈረው መልዕክት "የትግላችን አላማ ሀገራችንንና ራሳችንን ነጻነት ለማቀዳጀት ነው!!።" የሚል እና "ትግላችን በገዛ ሀገሩ ህይወት እየጨለመበትና ተስፋ እየቀረጠ ሀገሩን ጥሎ ሲሰደድ በረሀና ባህር እየበላው ወላጅ እናቱ የት እንደወደቀ ሳታውቅ በገፍ መርገፍ የጀመረውን ወጣት ሰቆቃ ለማስቆም የሚደረግ ትግል ነው!!።"፤ "ወያኔ ቢቃ!!፣ መለስ በቃ!! ፣ በወያኔ ስርአት በባርነት ከማለቅ የተለየ ነገር የለምና ለነጻነት ታገል!! የሚሉ ናቸው።

አፋኙ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በሺዎች የሚቆጠሩ የጸጥታ ሰራተኞችን፤ ፖሊሶችንና ሰቪል ለባሽ ወታደሮችን በየመንገዱና ጉራንጉሩ እያንቀሳቀሰ ባለበት በአሁኑ ሰዓት እንዲህ አይነት "የተነሱ" ጥሪ ወረቀት መበተን መቻል የሚያመለክተው አገዛዙ በቤተመንግሥት ዙሪያ ካሉት ምርጥ ታማኞቹ በቀር በሌሎች ብዙሃን እየተተፋ መሆኑን አመልካች ነው ተብሎአል።

ከምርጫ 97 ወዲህ በወያኔ አገዛዝ ላይ ተቃውሞአቸውን ለመሳማት እና ለለውጥ ለመታገል የሚፈልጉ ወጣቶች ቁጥር እየተበራከተ መምጣቱ ይነገራል።

## በአገሪቱ ውስጥ የሰፈነው የኑሮ ውድነት ከፍተኛ ደረጃ ላይ መድረሱን ዘረኛው መለስ ዜናዊ አመነ

የወያኔ ቁንጮዎች በአገዛዝ ዘመናቸው የተገኘ ስኬት ነው በማለት ያራግቡት የነበረው የ11 በመቶ አመታዊ የኢኮኖሚ እድገት ሚስጥር ምድር ላይ በሚታየው ድህነትና ጉስቁልና እርቃኑን መውጣት በመቻሉ የተደናገጠው መለስ ዜናዊ ከትናንት ወዲያ ማክሰኞ ለፓርላማ ተብዬው ሽንን ባደረገው ንግግር የአገሪቱ ፈታኝ እና ዋነኛው ችግር የኑሮ ውድነት መሆኑን ለማመን ተገዶአል።

ከአመት በፊት የኑሮ ውድነቱን የሚፈጥሩት ስግብግብ ነጋዴዎች ናቸው በማለት ሽማቹን ህብረተሰብና ነግዶ ተዳዳሪዎን ለማጋጨት አቅም የፈቀደለትን ሁሉ ተንኮል ሲፈትል የቆየው መለስ ዜናዊ "መንግስት የኑሮ ውድነቱን ለመቆጣጠር የተለያዩ እርምጃዎችን እየወሰድኩ ነው ቢልም የኑሮ ውድነቱ ግን እየባሰ፣ የምግብ ዋጋ እየጨመረ እና ዝቅተኛው የህብረተሰብ ክፍል እየተጎዳ ነው" በሚል ለቀረበለት ጥያቄ የኑሮ ውድነቱ የአገሪቱ አንገብጋቢው ችግር መሆኑን አምኖ ነገር ግን በተለመደው ቅጥፈቱ ችግሩ የተፈጠረው በአለም ገበያ መዋዠቅ ፣ የጅምላ ንግድ ስርጭቱ በሞኖፖል መያዝ፣ የገንዘብ አቅርቦት መጨመርና የዋጋ ትንበያ በመበራከቱ ነው በማለት ችግሮቹ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያቶች እንደተፈጠሩ አስመስሎ አቅርቦአል።

የሙስና እመቤት የሚል ቅጽል ሥም በተሰጣት ባለቤቱ አዜብ መስፍን የሚመራው ኤፈርት በአገራችን ውስጥ ያሉትን የጅምላ ንግድ ስርጭት ሙሉ በሙሉ ሊባል በሚችል ሁኔታ ተቆጣጥረውት ያሉ መሆናቸው እየታወቀና ለገንዘብ አቅርቦት መጨመርም ዋና ተጠያቂው እርሱ ራሱ ሆኖ እያለ እነዚህን እንደምክንያት ማቅረቡ ሰውየው እራሱ በፈጠራቸው ቀውሶች ምን ያህል ግራ እንደተጋባና መውጫ በሌለው ችግር ውስጥ ተዘፍቆ ያለ መሆኑን ያመለክታል ተብሎአል።

የአገሪቱ ኢኮኖሚ ከሚችለው በላይ ገንዘብ እየታተመ ገቢያ ውስጥ መሰራጨቱ እንዲቆም፤ የውጪ ምንዛሪ ክምችት እንዲቀንስና መንግሥት ከባንክ መበደሩን እንዲያቆም አለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅቶች አይ ኤም ኤፍና ወርልድ ባንክ በተከታታይ ሲወተውቱ እንደነበር የሚያስታውሱ አስተያየት ሰጪዎች፤ የተሰጣቸውን ሙያዊ ምክርና አስተያየት ወደ ጎን በመተው ልማታዊ መንግሥት መስሎ ለመታየት መለስ ዜናዊና ግብረአበሮቹ በአዲስ አበባ በመቀሌ ከተማዎች እንዲገነቡ ያደረጉዋቸው ትላልቅ ህንጻዎችም ሆኑ በተለያዩ ቦታዎች ተሰሩ የሚባሉ መንገዶች የህዝባችንን የኑሮ ጉስቁልና መደበቅ ባለመቻላቸው አገጠ በወጣው ድህነት የተማረረው ህዝብ አንድ ቀን ሆ ብሎ በመውጣት እንዳይውጣቸው ከፍተኛ ስጋት ላይ መውደቃቸውን ይናገራሉ።

## ዘረኛውና ፋሽስቱ መለስ ዜናዊ 99.9 በመቶ የሆኑት መምህራን በተደረገላቸው ደመወዝ ጭማሪ ተደስተዋል ፣የተቃወሙት ጥቂት፣ የማስተማር ብቃት የሌላቸውና ብጥብጥ እንዲያነሱ በተቃዋሚ ሀይላት በርቱ የተባሉ መምህራን ናቸው ሲል አሳፋሪ መግለጫ ሰጠ

የግንቦት 7 ዘጋቢ እንዳለው መለስ ለአጨብጫቢው ፓርላማ ሲገልጽ በአዲስ አበባና በአማራ ክልሎች ያሉ፣የማስተማር ብቃት የሌላቸው፣ ከሶስት በማይበልጡ ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ ጥቂት መምህራን ነበሩ ስራ ያቆሙት በማለት የመላ መምህሩን ጥያቄ አጣጥሎታል።

በማከልም በመምህራን ማህበር የቀረበ የደሞዝ ጥያቄ የለም ሲል ያገጠጠ ውሸት የዋሸ ሲሆን ለወያኔ ባላቸው ታማኝነት ተመልምለው ፓርላማ ውስጥ የተጎለቱት ካድሬዎቹ ሳይቀር ትዝብት ውስጥ እንደከተቱት የዘገበው የግንቦት 7 ዘጋቢ የመምህራን ማህበሩ እስከ ጥር 30 ቀን 2004 ዓ.ም የጊዜ ገደብ በማስቀመጥ በድሬ ደዋ ባካሄደው ጉባኤው የደሞዝ ጭማሪ ጥያቄ ማቅረቡ በግልጽ የሚታወቅ ሆኖ ሳለ፣ አሁን ስሙ ተቀይሮ የደሞዝ ማስተካከያ የተባለው ጭማሪም በዛ ጥያቄ መሰረት መሆኑ እየታወቀ እራሱን ምን ያህል ቢንቅ ነው እንዲህ አይነት ቅጥፈት የተሞላበት ንግግር በድፍረት የሚናገረው በማለት ብዙዎች እየተገረሙ እንደሆነ ገልጾአል።

የሙብት ጥያቄዎችን በአግባቡ መመለስን እንደ ሽንፈት የሚቆጥረው መለስ በሙብት ጥያቄው እንቅስቃሴ በንቃት የተሳተፉ መምህራንን የብቃት ማነስ በሚል የጥቃት ዒላማው በማድረግ ቀሪዎቹ መምህራን ሁለተኛ ጥያቄውን እንዳያነሱ ለማስፈራራት ሞክሯል።

በዚህም የአዲስ አበባና የአማራ ክልል ወላጆችና ተማሪዎች ለሙብት ጥያቄው በንቃት የተሳተፉትን ብቻ ለይተው እነዚህ መምህራን ብቃት የላቸውም ብለን ነበር፣በጊዜ እርምጃ ስላልወሰዳችሁ ይሄ ሁኔታ ተከስቷል ብለውናል በማለት አስተዛዛቢ ቅጥፈት መቀጠፉን ዘጋቢያችን ገልጿል።

መምህራኑ ተባረሩ ከተባለበት ትምህርት ቤት ዘጋቢያችን ያነጋገራቸው የአንድ የወላጅ ኮሚቴ አባል እኔ እኮ የወላጅ ኮሚቴ አባል ነኝ፣ ቢያንስ መረጃው ይኖረኛል፣የትኞቹ ወላጆችና ተማሪዎች መምህራኑ ብቃት የላቸውም እንዳሉ አልገባኝም፣ደግሞ እንዴት ከአዲስ አበባም ከአማራ ክልልም ብቃት የሌላቸው መምህራን ብቻ ተለይተው የሙብት ጥያቄ ያነሳሉ? ይህም ይሁን ብንል በሌሎች ክልሎች ያሉ መምህራን በሙሉ ብቃት አላቸው ማለት ነው?እንዲህ ከሆነ ደግሞ አዲስ አበባና የአማራ ክልል ተለይተው ደካማ መምህራን ለምን ተመደቡላቸው? የሚሉና ሌሎችም በርካታ ጥያቄዎች (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## በደቡብ ክልል የወያኔ ሹም የሆነው ሽፈራው ሽጉጤ አንድም ሰው ከክልሉ አልተፈናቀለም ሲል መግለጫ ሰጠ

በደቡብ ክልል በቤንች ማጂ ዞን ጉራፈርዳ ወረዳ ነዋሪ የነበሩ ትውልደ አማራ አርሶ አደሮች በግፍ መባረራቸው ሰፊ ተቃውሞ ከማስከተሉ ጋር ተያይዞ የወያኔ ሹሞች እርስ በርሱ የሚምታታና የሚጋጭ መግለጫ ከመስጠት አልፈው አንድም የተባረረ ሰው የለም እስከ ማለት መድረሳቸውን የግንቦት 7 ዘጋቢ ከስፍራው ገለጸ።

የክልሉ የወያኔ ፕረዝዳንት ሽፈራው ሽጉጤ በሰጠው ይፋ የሆነ የጽሁፍ ትዕዛዝ ከክልሉ የተባረሩ በሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎች ጉዳይ ጸሃይ የሞቀውና አለም ያወቀው ሃቅ ሆኖ እያለ ባለፈው ሳምንት መጨረሻ ላይ በክልሉ ሥር ለሚተዳደር መገናኛ ብዙሃን በሰጠው መግለጫ አንድም ሰው ከክልሉ የተባረረ የለም ብሎ መናገሩ ብዙዎችን እስቆጥቶአል።

የወያኔ ቁንጮዎችና በቅጥረኝነት ያሰማሩዋቸው እንደ ሽፈራው ሽጉጤ አይነቶቹ ሂሊና ቢሶች ህዝብ በአይኑ የሚያያቸውንና የሚዳሥሱ ወንጀሎች በአገሪቱና በዜጎቿ ላይ እየፈጸሙ ተግባራቸው ሲጋለጥ ሙልጭ አድረገው በመካድ ባህሪያቸው እየተመሳሰሉ መጥተዋል ያለው ዘጋቢያችን በአደባባይ የሚታየውን ገሃድ ሽምጥጥ አድርጎ መካድ በፊት የመለስ ዜናዊና በረከት ስምን ባህሪ እንደነበር እያደር ሲመጣ ግን ሃይለማሪያም ደሳለኝና ሽመልስ ከማል እንደወረሱት አሁን ደግሞ ሽፈራ ሽጉጤ ተኮትኩቶ እያደገበት መሆኑን አስመስክሮአል ብሎአል።

ከሳምንታት በፊት ቁጥራቸው 88 የሚሆኑ ሰፋሪዎች የአካባቢውን ደን በማውደማቸውና መሬትን በመሸጥ ህገወጥ ተግባር በመሰማራታቸው ተባረዋል ይሉ የነበሩ የወያኔ ባለስልጣኖች መልሰው አንድም የተባረረ የለም ለማለት የተገደዱበት ዋናው ምክንያት በአገሪቱም ሆነ በአለም አቀፍ (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

## የኢትዮጵያ ክርስቲያንና ሙስሊም ማኅበረሰብ በመለስ ዜናዊ አገዛዝ ላይ በአንድነት ይነሳ!

ሰሞኑን ከክርስቲያኑም ከእስልምና የሃይማኖት አባቶች ተመሳሳይ የትግል ጥሪዎች እየደረሱ ነው። ይህ በእጅጉ ተስፋ ሰጪ እና ተግባራዊ ምላሽ ሊሰጠው የሚገባው ተግባር ነው ብለን እናምናለን።

የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ስልጣን ከያዘበት ጊዜ ጀምሮ በኦርቶዶክስ ሃይማኖትና ቤተርስቲያን ላይ የማያቋርጥ ጥቃት ሲፈጽም መቆየቱ ይታወቃል። የኦርቶዶክስ ቤተክስቲያን ሲኖዶስዋ ለስደት የተዳረገባት በመለስ ዜናዊ የአገዛዝ ዘመን ብቻ ነው። የመለስ አገዛዝ የኦርቶዶክስ ክርስቲያኖችን የእምነት ነፃነት ተጋፍቷል፤ የሃይማኖት አባቶችንና ምዕመናንን ሰብዓዊ መብቶች ረግጧል፤ አሁን ደግሞ ይባስ ብሎ የዋልድባ ገዳም እና የቅዱሳን መካነ መቃብርን ደፍሯል። በቤተክርስቲያኗና በምዕመናኑ ላይ የሚያደርሰው የመብት ረገጣ እየከረረ በመምጣቱ ምዕመናን ጠንከር ያለ ምላሽ እንዲሰጡ የሃይማኖት አባቶች ጥሪ አድርገዋል። ይህ ጥሪ ወቅታዊና ተገቢ ነው ብለን እናምናለን።

የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በእስልምና ሃይማኖት ላይም የበረታ ጥቃት እያደረሰ ነው። አገዛዙ በእስልምና ሃይማኖታዊ አስተምህሮት ጉዳይ ጣልቃ በመግባትም ሙስሊሙን ማኅበረሰብ እርስበርስ ለማጋጨት ያደረገው ሙከራ ከፍተኛ ቁጣ አስከትሎ ለወራት የቀጠለው የሙስሊሞች መነሳሳትን ቀስቅሷል። የሙስሊሙ የእምነት ነፃነት ተደፍሯል፤ መሪዎቹን የመምረጥ መብቱ ተነፍጓል፤ የእምነት ተቋማቱ ነፃነት ተገፏል። የሙስሊም የሃይማኖት አባቶችም የኢትዮጵያ ሙስሊሞች በሞላ ለመብቶቻቸው እንዲቆሙ ጥሪ አድርገዋል። ይህ ጥሪ ወቅታዊና ተገቢ ነው ብለን እናምናለን።

በመለስ ዜናዊ የሚመሩ ቁጥራቸው እዚህ ግባ የማይባል የትግራይ ገዢ ጉጅሌ አባላት በመላ ኢትዮጵያ ላይ ከሃያ ዓመታት በላይ ሊፈነጩ የቻሉት የኢትዮጵያን ህዝብ በተለያዩ መንገዶች መከፋፈልና እርስ በርሱ በዓይነ ቁራኛ እንዲጠባበቅ ማድረግ በመቻላቸው ነው። መለስና ቡድኑ ሃይማኖትን የመሰለው የተቀደሰ ነገር እንኳን ሳይቀር ህዝብን ለመከፋፈያነት አውሏል፤ እያዋለም ነው። በተለይም ክርስቲያንና ሞስሊም ዜጎችን በማጋጨት የመለስ ቡድን ስልጣኑን አደላድሏል። ዛሬ ግን ሁኔታው በመቀየር ላይ ነው። አሁን ክርስቲያኑም ሞስሊሙም እኩል በመለስ ዜናዊ ፋሽስታዊ አገዛዝ እየተረገጠ መሆኑ በቀላሉ መረዳት የሚቻልበት ሁኔታ ተፈጥሯል።

በመለስ ዜናዊ የሚመራው የትግራይ ገዢ ጉጅሌ የኢትዮጵያ ክርስቲያንም ሙስሊምም የጋራ ጠላት መሆኑ በግልጽ እየታየ ነው።

መለስ ዜናዊ እና እኩይ ቡድኑ በሥልጣን ላይ እስካሉ ድረስ በአገራችን ውስጥ አንዳችም መብት፤ አንዳችም ነፃነት አይከበርም። የእምነት ነፃነት የሰብዓዊ መብቶች አካል ነው። የእምነት ነፃነታችንን ለማስከበር መለስ ዜናዊና ዘረኛ ቡድኑን ከሥልጣን ማስወገድ ግድ ይላል። ለዚህ ደግሞ የሁለቱ ታላላቅ ሃይማኖቶች አማኞች የጋራ ትግል መኖር ወሳኝ ነው።

የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ሙስሊም የክርስቲያኑ፤ ክርስቲያኑ ደግሞ የሙስሊሙ ማስፈራሪያ የሚያደርግበት እድል ሊሰጠው አይገባም። አገራችን ኢትዮጵያ ሁለቱ ሃይማኖቶች ተቻችለው፤ የሁለቱ ሃይማኖት አማኞች ተከባብረውና ተፋቅረው የኖሩባት አገር ናት። አሁን ደግሞ የሁለቱ ሃይማኖች አባቶች ለጋራ መብቶቻቸው መከበር በጋራ የሚሰሩበት ታላቅ እድል ተፈጥሯል።

የሁለቱ ሃይማኖቶች ምዕመናን ለጋራ መብቶቻቸውና ለጋራ አገር በአንድነት መቆማቸው በመለስ ዜናዊና ቡድኑ አማካይነት እየደረሰብን ያለውን አዋራጅ የባርነት ጊዜ ያሳጥራል፤ ወደ ነፃነት የምናደርገውን ጉዞ ያፋጥናል። ከዚህም በተጨማሪ ከመለስ በኋላ በምትኖረው ኢትዮጵያችን ውስጥም ህዝቧ ተቻችሎና ተፋቅሮ የሚኖር መሆኑ ከአሁኑ ማስተማመኛ ይሰጠናል።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ የሁለቱ ትላልቅ ሃይማኖት አባቶች ያደረጉትን የትግል ጥሪ ይቀበላል። መላው የኢትዮጵያ ህዝብም ጥሪዎቹን ተቀብሎ እንዲነሳ ያስተባብራል። ከዚህም በላይ የሁለቱ ሃይማኖቶች ምዕመናን በአንድነት በመለስ ዜናዊ ፋሽስታዊ አገዛዝ ላይ እንዲነሱ ጥሪ ያደርጋል።

ግንቦት 7፤ "ሃይማኖት የግል፤ አገር የጋራ ነው" በሚለው የቆየ ብሂል ያምናል። ከዚህም በላይ ግንቦት 7 "ሃይማኖት የግል፤ ነፃነት የጋራ ነው" ይላል። ስለሆነም ለሰብዓዊ መብቶቻችን መከበር፤ ለነፃነታችን ልዕልና የኢትዮጵያ ክርስቲያንና ሙስሊም በአንድነት ይነሳ ይላል።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

................................................................................................................................

## ዘረኛውና ፋሽስቱ መለስ ዜናዊ 99.9 በመቶ የሆኑት መምህራን በተደረገላቸው ደመወዝ ጭማሪ

. . . (ከገፅ 1 የዞረ)

ማንሳት ይቻላል። በመሆኑም ፈጠራው ማንንም ማሳሳት የሚችል አይደለም። ይልቁንም የወያኔ/ኢህዴግ አባል የሚሆኑት አብዛኞቹ ናቸው ብቃትና በራስ መተማመን የሚባል ነገር ያልፈጠረባቸው። እነዚህ የመብት ጥያቄ የሚያነሱትማ በሙያቸውና በራሳቸው ምን ያህል እንደሚተማመኑ በውስጣቸው የተሰገሰጉትን ካድሬ መምህራን ሳይፈሩ ተቃውሞአቸውን በአደባባይ በመግለጽ አስመስክረዋል ብለዋል።

የአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ ባባረራቸው መምህራን ማነስ ቅር እንዳለው የገለጸው መለስ በወላጆችና በተማሪዎች ስም ተጨማሪ የማባረር ርምጃ ለመውሰድ እየተዘጋጀ መሆኑን አመላክቷል።

በተጨማሪም መምህራን በስራቸው ለመቀጠል የብቃት ማረጋገጫ ሰርቲፊኬት እንዲኖራቸው የግድ ነው ያለው የወያኔው ቁንጮ በዚህ የወያኔ መለኪያ ተለክቶ ያላለፈ መምህር ከስራው እንደሚባረር ዝቶአል።

ስማቸው እንዳይገለጽ በመጠየቅ ለዘጋቢያችን አስተያየታቸውን የሰጡ አንዳ አንድ መምህራን ሲናገሩ የመለስ ዜናዊን ዛቻና የበቀል እርምጃ በአንድነት አሁኑኑ ካልታገልነው ነገ ሁላችንም አንድ በአንድ ተጠቂ እንደምንሆን መታወቅ አለበት፤ የብቃት ማረጋገጫ ሰርቲፊኬት የሚባለውም ለትምህርት ጥራት ታስቦ የተዘጋጀ ሳይሆን የወያኔ ድርጅት አባላት ያልሆኑ መምህራንን ለመምታት የተዘጋጀ በትር ነው።በመሆኑም ሁላችንም መምህራን የተባረሩት እንዲመለሱና ጥያቄያችን በተገቢው መንገድ መልስ እንዲያገኝ ትግላችንን መቀጠል አለብን ሲሉ አሳስበዋል።

ወያኔ ከዚህ በፊት የአሁኑን የአዲስ አበባ ከንቲባ ኩማ ደመቅሳን አቅም ማነስ በሚል ከኦሮሚያ ክልል ፕሬዘደንትነት አንስቶት ሆድ አደርነቱን መልሶ ሲያረጋግጥ የአቅም ግንባታ ሚኒስትር ደኤታ አድርጎ እንደሾመው ይታወሳል። ያገኘውን ሁሉ መናደፍን ስራዬ ብሎ የተያያዘው የወያኔ ስርዓት በዚሁ ወቅት የክርስትና እምነትና የእስልምና እምነት ተከታዮች በየበኩላቸው ሃይማኖታዊ መንግስት ለመመስረት እየሞከሩ ነው ሲል ወንጅሏል።

ኢትዮጵያ ውስጥ የአልቃይዳ ህዋስ ተገኝቷል፤ እነዚህ ደግሞ ሁሉም የሰለፊ እምነት ተከታዮች ናቸው በማለት የሌሎች እምነት ተከታዮችን በማስፈራራት ከጎኑ ለማሰለፍ ተፍጨርጭሯል።

የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮችንም አንድ ሀገር አንድ ሃይማኖት የሚል መፈክር አስተጋብተዋል፣በተለይም የማህበረ ቅዱሳን አባላት እንደ ሰለፊ እምነት ተከታዮች የሚታዩ ናቸው ሲል ኮንኗቸዋል።

ዘጋቢያችን ያነጋገራቸው አንድ የእስልምና እምነት ተከታይ በሰጡት አስተያየት መለስ የእስልምናና የክርስትና እምነት ተከታዮች መንግስቴን ለመጣል ይታገላሉ ሲል ከ90 በመቶ በላይ የሚሆነው የኢትዮጵያ ህዝብ የወያኔን ስርዓት ለመጣል እየታገለ ነው ማለቱ አልገባውም መሰለኝ፤በዚህ ደግሞ 99.6 ከመቶ የህዝብ ድምጽ አግኝቼ ነው ወደ ስልጣን የመጣሁት የሚለውን ቅጥፈቱን በራሱ ጊዜ እርቃኑን አስቀርቶታል ብለዋል።

ከዚህም ሌላ ፈረሱ እንዴት ይሮጣል ለሚል ጥያቄ ዓሳ ሙልጭልጭ ነው በሚል የመልስ ዘይቤ የሚታወቀው መለስ በወያኔ ፓርላማ ብቸኛው የተቃዋሚ ተወካይ አቶ ግርማ ሰይፉ ስለ ፖለቲካው ምህዳር መጥበብ፣የሰሞኑን የመድረክን የሙገር ሲሚንቶ አዳራሽ መከልከል በመጥቀስ ላነሱት ጥያቄ ከዚህ በፊት የሰጠኋችሁን ማስጠንቀቂያ እንደገና አጢኑት ሲል አስገራሚና ከጥያቄው ጋር አንዳች ግንኙነት የሌለው መልስ ሰጥቷል።

የአሁኑ የመለስ ማብራሪያ ከምንግዜውም በባሰ እጅግ አሳፋሪ ውሸቶች የታጨቀ መሆኑ ሰውዬው በጥልቅ እየዘቀጠና እየወረደ መሄዱን የሚያሳይ ከመሆኑም ሌላ እየደረሰበት ያለው ተቃውሞ ሁለገብነት መያዣ መጨበጫ እያሳጣው መምጣቱን የሚያመለክት ነው።

## በአገራችን ላይ የተከፈተውን የጠላት ዘመቻ ለማስቆም መፍትሄው መተባበር ብቻ ነው !!!

ትልቅ ጆሮ ያላቸው ግን ደግሞ በጥሞና ማዳመጥ የማይሆንላቸው፤ ትልቅ ዓይንም እያላቸው አርቀው ማየት የተሳናቸው እንስሶች አህዮች ናቸው። እነዚህ አህዮች ግን ማንነታቸውን የሚያጠፋ፤ ሥጋቸውን ለመቀራመት የመጣን ጅብ ለመከላከል ፊታቸውን ወደፊት አዙረው በኋላ እግራቸው ያን ጅብ በእርግጫ አጡዘው ከጥፋት የመዳን ልማድ አላቸው። ተፈጥሮ ከሚያስተምረን ብዙ ቁም ነገሮች መካከል አንዱ ይሄው ነው።

ዛሬ በአገራችን ታሪካችንን የሚጣፋ፤ ማንነታችንን የሚያዋርድ ኢትዮጵያዊያንንንም የማያውቅ፤ ሰማይንና ምድርን የሰራን እግዚአብሄርን የማይፈራ የውስጥ ጠላት ተነስቷል። ይህ ደመኛ ጠላት አገራችንን በታሪኳ አይታ የማታውቀው ቀውስ ውስጥ እየከተታት ነው። ይህ የውስጥ ጠላት ታሪካችንን ለማዋረድ ብርቱ ጥረት አድርጓል፤ ማንነታችንንም ሊያጠፋ ያልፈጸመው እኩይ ተግባር የለም። ምንም እንኳ አገራችን ብዙዎች የመሰከሩላት የረዥም ግዜ ታሪክ ባለቤት ብትሆንም ቀንደኛው ጠላታችን መለስ ዜናዊ "ኢትዮጵያ የምትባል አገር ታሪክ የላትም፤ ካላትም የአንድ ሽማግሌ እድሜ ታሪክ ነው ያላት" ማለቱን የምንረሳው አይደለም። በአገራችን ታሪክና በማንነታችን ላይ ጣቱን የቀሰረው ይህ ዘራፊና ዘረኛ ቡድን ቀጣዩን ጥቃት ደግሞ በእምነት ተቋማት ላይ አድርጓል።

በመጀመሪያ የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያንን አፍርሶ የራሱን ካድሬ በቤተ-ክርስትያን ራስ ላይ በመሾም የምእመናኑ አንድነት አፈረሰ ከዚያም ቤተክርስትያን የሌቦችና የቀማኞች ዋሻ በመሆኗ የአንዲት ቤተክርስትያን ልጆች ከሁለት ጎራ በላይ ተከፈሉ።

ይሄን ተከትሎ በርካታ የታሪኮቻችንን ትላልቅ ቅርሶችና መዛግብትን የያዙ ለዓይኖቻችን ማረፊያ፤ ለጆሮአችንም ብዙ ድንቅ ነገር የምንሰማባቸው በዓለም ታውቀውና ክበር ተሰጥቷቸው የቆዩ አድባራትን ማፍረስ ጀምሯል። የምእመናኑንም አጽም አውጥቶ ሜዳ ላይ በመጣል መሬቱን ለሸንኮራ አገደ ልማት በማለት ለባእዳን አሳልፎ እየሸጠ ነው። ይሄ የጠላት ተግባር እንጂ ለአገሩ ክብር የሚቆረቆር ቡድን ተግባር አይደለም። አብዛኛው የአገራችን ታሪክ የተቆራኘው ዛሬ መለስ ዜናዊ እየነጠቀ ለሸንኮራ አገዳ ልማት በሚል ሰበብ እየቸበቸበ በሚገኘው የአድባራቱ መሬት ላይ ነው። ለመለስ ዜናዊና ጀሌዎቹ የታሪካችን አምዶች ከሸንኮራ አገዳ አይበልጡምና የአገሪቷ የታሪክ ቅርሶች የቆሙበትን መሬት በሙሉ ማጥፋት መለስና ጉጅሌዎቹ የቆሙለት ቋሚ ተልእኮ ነው።

ምንም ዓይነት እምነት ብንከተል ዛሬ መለስና ጉጅሌዎቹ ሊያወድሙት የተነሱት ገዳማት የማንነታችን መገለጫዎች በመሆናቸው ሃብቶቻችን መሆናቸውን መገንዘብ ያስፈልጋል።

መስጊዶቻችንም እንደ አድባራቱ ሁሉ ብዙ ድንቃ ድንቅ ታሪኮቻችንን የያዙ ናቸው። ዛሬ መለስ ዜናዊና ዘረኛ ቡድኑ በሙስሊሙ ማህበረሰብ ላይ ተሰምቶ የማይታወቅ ዘመቻ ጀምረዋል። አንዱን ጥሩ ሙስሊም ሲሉ፤ ሌላኛውን ደግሞ ከጽንፈኛ አሸባሪዎች ጋር እያስተሳሰሩ በዜጎች ላይ የሚያድረሱት ግፍ ከግዜ ወደ ግዜ ከምን ግዜውም በላይ ተጠናክሮ ቀጥሏል። የእምነት ነጻነታችን ይከበር ያሉ ሙስሊሞችን ጽንፈኛ አሸባሪዎች ናቸው ማለት መለስ ዜናዊና ጀሌዎቹ የደረሱበትን የአሸባሪነት ደረጃ የሚያመለክት ነው። መለስ ዜናዊ ሙስሊሙን ማህበረሰብ ለሁለት ከፍሎ ሁከት የሚፈጥረው በአጣቃላይ በኢትዮጵያዊያ ላይ ካለው ጥላቻ የመነጨ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።ሙስሊሙ ማህበርሰብ ጎሳ ለይቶ ርስ በርሱ የማይጋጭ፤ በጎሳ ከመከፋፈል ይልቅ አንድ መሆን ይሻለናል የሚል ጠንካራ እምነት ያለው ማህበረሰብ ነው።መለስ ዜናዊ የሚጠላው እና ሊያተራምሰው የተነሳውም ይሄን የረጋ አንድነት ነው።

ህዝቦች አንድ የሚሆኑበት ነገር ለዘረኞችና ለዘራፊዎች ቅዥታቸው ነው።ይሄ ቅዥታቸው በሚችሉት ሁሉ አንድነቱን አናግተው ያን ህዝብ አዋርደውና ረግጠው ለመግዛት ብዙ እኩይ መንግዶችን እንድሄዱ አድርጓቸዋል። እነመለስ ዜናዊ የሚሄዱባቸው የጥፋት መንገዶች አገራችንን የከፋ ሁከት ውስጥ የሚከቱ መሆናቸውን ይህን ዘረኛና ዘራፊ ቡድን እየተከተሉ ያሉ ኢትዮጵያዊያን ሊገነዘቡት ይገባል።

ዛሬ አገራችን ባለችበት ሁኔታ ከልዩነቶቻችን ይልቅ ማንነታችንን ሊያጠፋ፤ ደማችንንም በከንቱ በየሜዳው ሊያፈስ የተነሳው ጠላት እጅግ የከፋ ነው።መብታችንን በጠይቅን ግዜ አሸባሪ ብሎ የመከራ እንጀራን ሊያበላን፤ የመከራ ጽዋንም ሊያጠጣን የተነሳ ኃይልን ለሃያ ዓመታት በጫንቃችን ላይ ተሸክመነው ኑረናል። ይሄ ዘረኛና ዘራፊ ቡድን በቃህ የሚባልበት እውነተኛው ግዜ አሁን ነው። በክርስትያኑ እንባ ሙስሊሙ አይስቅም፤ በሙስሊሙ እንግልትም ክርስትያኑ ደስ አይሰኝም። ክርስትያንና ሙስሊሙ አንድ ላይ በመቆም ፍትህ የነገሰባት፤ ነጻነት የሰፈነባት፤ የህግ የበላይነት የተከበረባት፤ ዜጎች በሙሉ ከጎሳ ቆጠራ ወጥተው በገዛ አገራቸው በህግ ማእቀፍ ሥር የፈለጉትን እምነት ተከትለው የሚኖሩባትን አገር ለመፍጠር በጋራ መሥራት ይጠበቅባቸዋል። ይህን ህያው ጠላት በቃህ ለማለት መሰባሰብ፤ ከልዩነት ይልቅ የጋራ ጠላት ላይ ማተኮር፤ ራስን ብቻ ሳይሆን ሌላውንም ለመከላከል አብሮ መቆም ግዜው የሚጠይቀው ታሪካዊ ግዴታ ነው። ምንም ከማይገኝባት ከዚያች አህያም መማር ያለብን እውነት በጋራ ሆኖ አንድ ላይ ገጥሞ ጠላትን መመከትን ነው።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ ይሁን !!!**

## በልማት ሥም የዋልድባን ገዳም ለማፍረስ እየተካሄደ ያለው እንቅስቃሴ በገዳሙ የተጠለሉትን አባቶች እጅግ እያሳሰበ ነው

ለስኳር ምርት የሚሆን አገዳ ለማምረት በሚል ሰበብ በታሪካዊነቱና በጥንታዊነቱ የሚታወቀውን የዋልድባ ገዳምን ለማፍረስ ወያኔ እያካሄደ ያለው እንቅስቃሴ ገዳሙ ውስጥ ተጠልለው በሚኖሩ አባቶችና በክልሉ ህበረተሰብ ከፍተኛ ተቃወሞ የገጠመው ቢሆንም መንገድ የሚሰሩ ቡልዶዘሮችና ግሬደሮች መሰማራታቸውን ለማወቅ ተችሎአል።

ለልማት ተብዬው ፕሮጀክት የተጀመረው የደን ምንጣሮና የመንገድ ሥራ ከገዳሙ በእግር አንድ ሰአት ድረስ ተቃርቦአል የሚሉ የገዳሙ መነኮሳት አሁን በተጀመረው ሁኔታ ገዳሙ ቤተክርስቲያኖች ያረፈበት ድረስ ከመዝለቅ እንደማይመለስ በስጋት እየተናገሩ ነው። የዋልዳብ ገዳም ላይ እየተወሰደ ያለውን ውድመት ለአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮ የተናገሩት አባት በመንግሥት ጳጥታ ሃይሎች አሁንም እየተፈለጉ እንደሆነ የሚናገሩት ምንጮች የክልሉ የወያኔ ባለስልጣናትም ሆኑ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን የአገር ውስጥ ሲኖዶስ ጉዳዩን አየትው እንዳላዩ ዝም ብለውታል በማለት ያማርራሉ።

እንደ ምንጮቻችን መረጃ የአካባቢውን ህዝብ እጅግ እያሳዘነ የመጣው በተለይም የገዳሙን ህልውና የመጠበቅ ተቋማዊ ሃላፊነት ያለባት የኦትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የአገር ቤት ስኖዶስ ከወያኔ ጋር በማበር በገዳሙ ላይ የተቃጣ ምንም አይነት አደጋ የለም በሚል ጭፍን ማስተባበያ ላይ ማተኮሩ የሲኖዶሱን መንፈሳዊ ተቋምነት ጥርጣሬ ውስጥ እየከተተው መጥቶአል ።

ወያኔ ስልጣን ከተቆጣጠረበት ጊዜ ጀምሮ የቤተክርስቲያኒቱ ጳጳስ ሆነው የተሾሙት ፓቲሪያርክ ማንነትና መንፈሳዊነት ሲያነጋገር የቆየ ቢሆኑም ከሰውዬው ጋር ያሉ ጳጳሳት እንዲህ አይነት ጥፋት በቤተክርስቲያኒቷ ቅርስና መንፈሳዊ ቦታ ላይ ሲደርስ ዝም ብለው ይመለከታሉ የሚል እምነት በብዙ ምዕመናን ዘንድ ሳይኖር መቆየቱ ይታወቃል።

በዋልድባ ገዳም ውስጥ ያሉ 18 በቴክርስቲያኖች በዚህ የወያኔ ልማት ተብዬ ፕሮጀከት እንደሚፈርሱ መረጃ የደረሳቸው መነኮሳት ህዝቡ ተረባርቦ አድባራቱን ከመፍረስ እንዲያድን እየተማጸኑ ነው እንደሆነ ይታወቃል።

በስደት ላይ የሚገኘው ሲኖዶስ በዋልድባ ገዳም ላይ የሚደረገውን ጥፋት በጽኑ በማውገዝ ህዝበ ክርስቲያኑ ዝም ብሎ እንዳይመለከትና የአገሪቱን ሉአላዊነት ከመናድ አላማው ጋር ተከብረው የኖሩትን የአገሪቱን መንፈሳዊ ገዳማት በማፍረስ ተልዕኮ ላይ የተሰማራውን የወያኔ አገዛዝ ሁሉም የአገሪቱ ዜጋ ተባብሮ እንዲታገል ጥሪ ማስተላለፉ ይታወሳል።

## በደቡብ ክልል የወያኔ ሹም የሆነው ሽፈራው ሽጉጤ አንድም ሰው ከክልሉ አልተፈናቀለም . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

ህጎች ዜጎች በአገራቸው ውስጥ ተዘዋውረው ሲኖሩ ለሚፈጽሙት ወንጀል በህግ ይጠየቃሉ እንጂ ሊባረሩ አይገባም የሚል የጠነከረ ተቃውሞ ስለተነሳባቸው እንደሆነ ዘጋቢያችን ያነጋገራቸው አንድ የክልሉ ባለሥልጣን ገልጸዋል።

ሽፈራው ሽጉጤ አፍቃሬ ወያኔ ለሆነ አንድ የፓልቶክ ስብስብ በወዲያኛው ሳምንት ቅዳሜ በሰጠው ቃለመጠይቅ የተባረሩ ሰዎች መኖራቸውን አምኖ ቁጥራቸው ግን የተጋነነ መሆኑን ገልጾ እንደነበርና ተባራሪዎቹ በህገወጥ መንገድ የሰፈሩና ደን በማውደም ተግባር ሲሰማሩ የተያዙ ናቸው ብሎ እንደነበር መዘገቡ ይታወሳል።

ከጉራፈርዳ ወረዳ የተባረሩ አማሮች ጉዳይ በአገር ውስጥና ከአገር ውጪ ከፍተኛ ተቃውሞ በማስነሳቱ ምክንያት ሁኔታውን የሚያጣራ አንድ ቡድን ተሰደው አዲስ አበባ የመጡትን ተፈናቃዮች አስገድዶ ወደ የትውልድ ስፍራቸው በማጓጓዝ ከተሳተፈው ብአዴንና ከደቡብ ክልል ተውጣጥቶ የማጣራት ሥራውን ጀምሮ እንደነበር በሰፊው ተዘግቦ እንደነበር ይታወቃል።

## ወያኔ ኢህአዴግ በቅርጽ ካለሆነ በስተቀር፣ በይዘት ከደረግ ጋር አንድ መሆናቸውን የአንድነት ልሳን የሆነው ፍኖተ ነጻነት ጋዜጣ ገለጸ

ከአቶ መለስ አገዛዝ እውነተኛ የመድበለ ፓርቲ ሥርዓት መጠበቅ በፍጹም አይቻልም፡፡የወያኔ /ኢህአዴግ አቋም ግልጽ ነው፡፡ ተቃዋሚዎች እግር እስኪያወጡ መጠበቅ፣ እግር ሲያወጡ መቁረጥ የሚል ነው ። የሰሞኑ የሰላማዊ ታጋዮች እስርም የዚሁ እግር ቆረጣ ፖሊሲ ውጤት ነው በማለት አንድነት በልሳኑ አብራርቷል።

እንደ ጋዜጣው አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ፣ አንድነት/ መድረክና ሌሎች ሀቀኛ ተቃዋሚዎች በወያኔ ኢህአዲግ ከጦርነት ያለተናነሰ ዘመቻ እየተካሄደባቸው ነው፡፡ በተለይም የደህንነት ተቋሙ የሀገርን ጥቅም ለማስጠበቅ ከመስራት ይልቅ በተቃዋሚ ፓርቲዎች ቢሮ አከባቢ ጀሌዎቹን በመበተን እንደ ስራ ፈት ተገትረው እንዲውሉ እያደረገ ነው። ስራቸውም የየፓርቲዎቹን አመራሮች ስልክ መጥልፍና ማን ምን አለ የሚል ወሬ መለቃቀም ነው።

እውቅና አግኝተው፣ በህጋዊ መንገድ የሚንቀሳቀሱ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ከህዝብ ጋር ተቀራርበው እንዳይወያዩ በርካታ መሰናክሎች አሉባቸው፣ ለዚህም አንድነት/ መድረክ ባለፉት ሶስት ወራት ህዝባዊ ስብሰባ ለማድረግ ያደረገው ተከታታይ ጥረት በወያኔ እንዳይሳካ መደረጉ ከብዙዎቹ መሰናክሎች አንዱና ለምሳሌነት ሊጠቀስ የሚችል ነው ፍኖተ ነጻነት እንዳለው።

እስከመቼ ዴሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶች ተጣሱ እየተባለ ሲጮሆ ይኖራል? እስከ መቼ አንቀጽ እያጠቀሱ በጋዜጣዊ መግለጫ ተገድቦ መኖር ይቻላል? መሠረታዊ የመደራጀትና የመሰብሰብ መብት በግልጽ ከተናደ፣ በህጋዊ ፓርቲ ተመዝግበን እየሠራን ነው በሚሉትና በህቡዕ እየሰሩ ነው በሚባሉ ፓርቲዎች መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው? በማለት የሚጠይቀው የአንድነት ልሳን ሰላማዊ ትግሉን ከገባበት የውድቀት አዙሪት አውጥቶ ለድል ለማብቃት ከፍተኛና ብዙ ያልተሞከሩ ስራዎች መሰራት አለባቸው ብሏል።

የቤት ለቤት ቅስቀሳና በየሜዳው ሕዝብን የማወያየት ስራዎች በፋጣኝ መጀመር ያለባቸው ስልቶች ናቸው፡፡ የፓርቲውን አቅም የማጠናከር ስራዎች፣ ከሌሎች ሀቀኛ ተቃዋሚ ድርጅቶች ጋር በቅንጅት ወይም በመዋሃድ መስራትና ግልፅ የሆኑ አማራጭ ፖሊሲዎችን ነድፎ መንቀሳቀስም እንዲሁ አንገብጋቢ የወቅቱ ጥያቄዎች ናቸው ነው የሚለው አንድነት በልሳኑ፡፡

ትግሉን ከተከላካይነት አውጥቶ ወደ አጥቂነት ማሸጋገር ግድ ይላል በማለት በልሳኑ ፍኖተ ነጻነት አጽንዖት የሰጠው አንድነት የህዝቡ ልብ ውስጥ ለመስፈር ማንኛውንም ዓይነት መስዋትነት ለመክፈል መንቀሳቀስን በእጅጉ አስፈላጊ ብሎታል፡፡

በማያያዝም የደርግ አገዛዝ ተወግዶ፣ ህገ-መንግስታዊ አሰራርና መድብለ ፓርቲን የምር የተቀበለ ሥርዓት ይመሰረታል የሚል የብዙ ኢትዮጵያውያን ምኞትና ተስፋ ነበር፡፡ ኢትዮጵውያን ለአንዴና ለመጨረሺያ ጊዜ ከጥላቻ ፖለቲካና ከመገዳደል ወጥተን፣ በሃሳብ የበላይነት ላይ የተመሰረተ ሥልጡን የፖለቲካ እንቅስቃሴ እናደርጋለን የሚል ራዕይ ነበረን፤ ያ ሁሉ ግን ዛሬ ወይቧል ፤ለዚህ ደግሞ በትግሉ ሂደት፣ ቀላል የማይባሉ ወገኖች የሰለማዊዉን መስመር በመልቀቅ ወደ ሁሉን አቀፍ አማራጭ መሄዳቸው አንዱ ማሳያ ነው ሲል ፍኖተ ነጻነት አብራርቷል።

ይህ የአንድነት መግለጫ ዘረኛው የወያኔ ስርዓት ምን ያህል እየከፋና እየዘቀጠ፣እፈናና ጥላቻው ስር እየሰደደ እንደመጣ የሚያመላክት ነው። እናም የህዝብ ወገን ነን የሚሉ ተቃዋሚዎች በበኩላቸው በተቻለ መጠን ልዩነቶቻቸውን በማቻቻል ይህንን ዘረኛ፣ የመከራና የጥላቻ አምራች የወያኔ ስርዓት ለመገርሰስ መረባረብ አለባቸው ያሉት ደግሞ አንድ የተቃዋሚ ድርጅት አባል ናቸው።

## የጀግና ምክር

ልጆች የልጅ ልጆች ውስጠም ውጭ ያላችሁ
ካለየኹት ከታዘብኩት ትንሽ ላማክራችሁ
ልፊያ ብሎ ነገር ትግል ይቅርባችሁ
ፈሪ ለእናቱ ነው ጎመን በጤ ናችሁ
ቀኛችሁን ስጡ ሲመታ ግራችሁ

በመንግስቱ ንዋይ አባቴ የሞተው
ልጆቼ ያለቁት ኢሐአፓ ተብለው
በምርጫ ኢህአዲግ የልጅ ልጅ ያጣነው
ዝም በሉ የሚለን መካሪ አጥተን ነው

ዝም በሉ የሚለን መካሪ ሰው አጥተን
ቱርክና ድርቡሽን ጣሊያንን አባረረን
አዳዲስ ጅብ እንጂ ሌላ ምን አገኘን

የወሊጋው አብዲሳ የነጃሙ በላይ
አሉላ አባ ነጋ የትግራዩ ዘርዓይ
ጀግናው አቡነ ፔጥሮስ ወይ መንግስቱ ንዋይ

እነአብርሃም ደቦጭ ወይ ጥላሁን ግዛው
ፍትህ ፍትህ ብለው የቀሩት ሜዳ ላይ
ዝምበሉ የሚላቸው ጠፍቶ ነው አስተዋይ

ስለዚህ ልጆቼ እኔ የምመክራችሁ
ሰልፍ ብሎ ነገር ተቃውሞ ይቅርባችሁ
ፈሪ ለእናቱ ነው ጎመን በጤናችሁ
ቀኛችሁን ስጡ ሲመታ ግራችሁ
እሱ ያለው ላይቀር ምን አደከማችሁ?

ዛሬ እንደሚታየው ኅበዙ ምሁሩ
የነጻነት ትርጉም ሲገባው ሚስጢሩ
በአራቱም አቅጣጫ ወጥቷል ከሃገሩ
ልጆቼ ብልጥ ሁኑ ካለፈው ተማሩ
በቦሌም በባሌ በእግርም ባየሩ
መሄድ ነው ወደሌላ ሲከፋ ሃገሩ
ቁጥራቸው ብዙ ነው ተሰድደው የከበሩ
ወላጆች የጦሩ አምስት ቤት የሰሩ

ከአረቦቹ አገር በዜና የምንሰማው
ችግሩ ቢከፋም የባዕድ አገር ጣጣው
በዲቪ ሎተሪ ስንቱ ነው የወጣው

ባህር ውስጥ ቢሰምጡም በመርከብ ሲጠፉ
ያለቪዛ ገብተው ታስረው ቢገረፉ
በስደተኛ ካምፕ አመታትም ቢያልፉ
ከርቸሌ ከመግባት አጓጉል ሲጋፉ
በእግራችሁም ቢሆን ተሰደዱ ጥፉ
ላልሰሙት ንገሩ ልጆቼ አትስነፉ

ትዳሩን ስራውን ቤቱን እየጣለ
ማነው ያልተሰደደ ማነው ያልኮበለለ
በኤርትራ ጦርነት ሲያሰቸግር ሻእቢያ
የኢህአዴግ ጀኔራል ሲገዛ መሳሪያ
ከሻንጣ ዶላር ጋር ቢላክ ራሺያ
በዚያው ቀረ አሉ ሳይመጣ ኢትዮጲያ

የካቶሊኩ ቄስ ጭምቱ ፓስተሩ
ቢላኩ ቫቲካን ሰው እንደያስተምሩ
ምናቸው ሞኝ ነው እንደወጡ ቀሩ

እንኳን አንተ ደሃው መናጢው ቅርና
ግርማ ወልደጊዮርጊስ ድንገት ታመሙና
ወደ አረብ አገር ሄደው ለህክምና
አልመለስ አሉ መች ተሻለኝና

ኢትዮፒያዊውም ዶክተር ይዛቸው የሄደው
በዚያው ጠፋ አሉ እሳቸው ተኝተው

አዳምጡኝ ልጆቼ መሰደድ ፋሽን ነው
ገዳም ሊያሳድሱ እርዳታ ሰብስበው
ለነፍሴ ይሆናል ይጠቅመኛል ብለው
በ6 ወር ቪዛ ወደ እስራኤል ሄደው
እማሆይ ቀሩ አሉኝ አሳይለም ጠይቀው

ወደ ጀርመን አገር ሰርግ ተጠሩና
ከነአቴቴአቸው ወጥተው ከቀበና
መቼ ተመለሱ ወይዘሮ ባፈና?

ሙስሊም ኅረቤቴ ሃጂ ኡምራ ሄደው
መካ መዲና ላይ የደንቡን አድርሰው
ለምን በዚያው አይቀሩ ደረሰ ነኝ ብለው?
ናተንኛሁ ሆኖ ጎንደሮች ስማቸው
እስራኤል አልሄዱም ሰልፍ ሰልችቷቸው?

ቴሬሪስት ሲሉት በዩጋንዳ ወጥቶ
የአባ ጅፋሩ ልጅ ጂማ አጋሮን ትቶ
ቱትሲ ነኝ አላለም ሩዋንዳ ገብቶ?

እንኳን አንተ ደሃው ያልተማርክ ምስኪኑ
አብራሪው ፓይለቱ ጠፍቶ ካፒቴኑ
ሮም ላይ አልቀረም ጀቱ አውሮፕላኑ?
ባፋኑኩሎ የሚለው ተሸሎት ጣሊያኑ

እንኳን ስራ አጡ የሚበላ የሌለው
የመለስ ጠባቂዎች ለስልጠና ሄደው
መለስን ከማጀብ መሰደድን መርጠው
ዩክሬይን አልቀሩም ኮማንዶ ተምረው?

የህዳሴ ወከባ ከበሮው መዝሙሩ
የቦንዱ ገበያ ጫረታው ባዛሩ
አልገባ ቢላቸው ጠፍቷቸው ምስጢሩ
በአባይ ግድብ ዙሪያ እንዲደራደሩ
ከተላኩት መሃል ሶስቱ ግብፅ ቀሩ

ዳላስ ብወስዳቸው አያቱ ናፍቀውኝ
ግሪን ካርድ ካልያዝኩኝ ሲቲዝን ካልሆንኩኝ
አሻፈረኝ አሉ እኔ መች አበድኩኝ

እንኳንስ አንተና ኅልማሳው ወጣቱ
ኮሎኔል አብረሃም የዘጠና ዓመቱ

አሜሪካ ሄደው የልጅ ልጅ ሊድሩ
እንኳን ሊመለሱ ወዲህም አልዞሩ
ሰርቶ በላ ወዛደሩ ባላገሩ አርሶ አደሩ
ያልተማሩ የተማሩ ያስተማሩ የሚማሩ
ለነፃነት መናገሩ ተቆጭቶ ስላገሩ
ባደገበት በሰፈሩ በኖረበት በመንደሩ
ሲበዛበት መገረፉ ሳያጠፉ መታሰሩ
ተሰፋ ሲቆርጥ በባንዲራው በሃገሩ
ለምን አይሰደድ ባዶ አይቀር መንደሩ

ለምን አይሰደድ ለምን ዲቪ አይሞላ
ያለፍርድ ሲታሰር ያለ ክስ ሲጉላላ

እንከን የተማረው ድግሪ ያለው ቀርቶ
ገበሬው ተሰድዶ ባገር ተስፋ ቆርጦ

አተይዩም እንዴ ማሳው ባዶ ቀርቶ?
ለሁሉም ልጆቼ ውስጠም ውጭ ያላችሁ
ካየሁ ከታዘብኩት ትንሽ ልምክራችሁ
ፍትህ ብሎ ነገር ምን ሊሰራላችሁ?
ፈሪ ለእናቱ ነው ጎመን በጤ ናችሁ
ቀኛችሁን ስጡ ሲመታ ግራችሁ

### የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።

<u>መካከኛ ሞገድ</u>:- በ 358 MB, በ 837 kHz
<u>አጭር ሞገድ</u>:- በ 31 MB በ 9700 KHz
በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz
በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሚም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቄያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

<u>ማሳሰቢያ</u>:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

### ውድ አንባቢዎቻችን

ለፕሮግራማችን ይበጀል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዣችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org